Legal Aid Society OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MAKING JUSTICE REAL

# የዲስትሪክቱ የህዝብ ጠቀሜታዎች
# በኮቪድ-19 (COVID-19) በሽታ ወቅት

(ጥቅምት 4 ቀን 2021 የተሻሻለ)


የገንዘብ እርዳታ (Cash Assistance) ........................................................................................ 2

በኮቪድ COVID-19 ምክንያት ስራዬን አጥቻለሁ። ለስራ ለወጡ ከሚሰጠው የስራ መውጣት ክፍያ (unemployment benefits) ሌላ፤ የምግብም ሆነ ሌሎች ውጪዎችን የሚሸፍን የሚሰጥ እርዳታ አለን ? ............................................. 2

በኮቪድ ምክንያት ስራዬን አላጣሁም ግን በቀን የምሰራባቸው ሰዓቶች ተቀንሰውብኛል።አሁን የማገኘው ገቢ ጎድሏል። አሁንም የስናፕና የቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ SNAP/TANF እርዳታ ላገኝ እችላለሁን? ............................................................ 3

የስናፕና የቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (SNAP እና TANF) ጠቀሜታዎች እስኪጀመርልኝ ስንት ግዜ ይፈጃል ? ............................ 3

የስናፕና የቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (SNAP እና TANF) ጠቀሜታዎችን ማግኘት ስጀምር፤ ሌላ ገቢ ማግኘት ጀመርኩ፤ የጀመርኩትን የስናፕና የቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (SNAP እና TANF) ማግኘቴን እቀጥላለሁን?......................................................... 4

ለስናፕና ለቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (SNAP እና TANF) ሳመለከት ችግር ቢያጋጥመኝ የት ነው የምደውለው?.......................... 4

የጤና ኢንሹራንስ (Health Insurance)........................................................................................ 5

ስራዬን ሳጣ፤ የጤና ኢንሹራንሴንም አብሬ አጣሁ።የህዝብ የጤና ኢንሹራንስ ለማግኘት ላመለክት እችላለሁን?.................. 5

ለኢንስታካርት (Instacart) እቃ የማመላለስ ስራ በመስራት ትንሽ ገቢ ባገኝ፤ ግን የጤና ሽፋን ኢንሹራንስ የነበረውን ስራዬን ሳጣ ኢንሹራንሴም አብሮ ስለሄደ፤ ሜዲኬድ ወይም አላያንስ ለማግኘት አሁንም ብቁ እሆናለሁን ? ...................................... 6

የጤና ኢንሹራንሱ እስኪጀምር ድረስ ምን ያህል ግዜ ይፈጃል? ......................................................................... 6

ሜዲኬድ ማግኘት ስጀምር፤ ሌላ ገቢ ማግኘት ጀመርኩ፤ ሜዲኬድ ማግኘቴን እቀጥለሁን? ........................................ 7

የጤና ኢንሹራንስ እንዳገኝ የት ነው ማመልከት የሚገባኝ? ............................................................................. 7

የስንክልና እርዳታ (Disability Assistance) ............................................................................... 7

ስራ መስራትን እጅግ ከባድ የሚያድረግ ስንክልና አለብኝ፤ ሊረዱኝ የሚችሉ ምንጮች አሉን? ..................................... 7

ያለኝ ስንክልና ቀኑን ሙሉ ለመስራት አዳጋች የሚያደርግብኝ ቢሆንም አንዳንድ ቀዳዳ መሸፈኛ ገቢ ለማግኘት ግን በከፊል ግዚያት ግን ልሰራ እችላለሁ። ይህም ሆኖ የSSI ወይም የSSDI እርዳታ ማግኘት እችላለሁን?............................................. 8

ከ SSI፤ SSDI፤ ወይም IDA ክፍያ ማግኘት መጀመር ምን ያህል ግዜ ይፈጃል?................................................... 9

ለ SSI፤ SSDI፤ ወይም IDA ሳመለክት ችግር ካጋጠመኝ የት ነው ይምደውለው? ................................................ 9

የስደተኞች ህዝባዊ ጠቀሜታ ለማግኘት የሚያስፈግ የብቁነት መለክያ ..................................................................... 9

የአሜሪካን ዜጋ አይደለሁም፤ ህጋዊ የሆነ ቪዛ ወይም የስራ ፈቃድ የለኝም። ቀደም ሲል ለተገለጹት የእርዳታ ፕሮግራሞች (ለምሳሌ ለSNAP፣ ለTANF፣ ለጤና ኢንሹራንስ ወይም ከስንክልና ጋር የተያያዘ እርዳታ) ብቁ ልሆን እችላለሁን?........................ 9

ከሚሰጡት እርዳታዎች ውስጥ አንድ እንኳን ብቀበል፤ በዚህ (public charge rule) መሰረት አንጻሬ ሊሰራ ይችላልን? .....10

## የገንዘብ እርዳታ (Cash Assistance)

**በኮቪድ COVID-19 ምክንያት ስራዬን አጥቻለሁ። ለስራ ለወጡ ከሚሰጠው የስራ መውጣት ክፍያ (unemployment benefits) ሌላ፤ የምግብም ሆነ ሌሎች ውጪዎችን የሚሸፍን የሚሰጥ እርዳታ አለን ?**

ለስናፕ (SNAP) አብዛኛውን ግዜ ፉድ ስታምፕ (food stamps) በመባል ለሚታወቀውና ለተቸገሩ ቤተሰቦች የሚሰጥ ግዚያዊ እርዳታ ለ (ቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (TANF) ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። (ቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ TANF) ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ቤተሰቦች፣ 18 ወይም ከዛ በታች ዕድሜ ላላቸው ልጆችና ለነፍሰጹሮች በጥሬ ገንዘብ የሚሰጥ እርዳታ ነው።

ኦንላይን በመግባት online ማመልከት ይችላሉ። ለዚህም የዲሲ አክሰስ ሞባይል አፕን (DC Access mobile app) ይጠቀሙ። (በእንግሊዘኛ፣ በስፓኒሽና በአማርኛ ቋንቋዎች) የተዘጋጀ ማመልከቻዎን ሞልተው ወደ አገልግሎት ማእከል (ቁጥሩ ከታች አለ) ፤ በፋክስ ይላኩ ወይም በአካል ወደ መስርያ ቤቱ ሂደው መስጠት ይችላሉ። ይህ ግን በወቅቱ ባለው የኮቪድ በሽታ ምክንያት የተደገፈ አይደለም።

> ኮንግሬስ ሃይትስ የአገልግሎት ማእከል (Congress Heights Service Center)
> 4049 South Capitol St., SW
> የስልክ ቁጥር: (202) 645-4546
> ፋክስ: 202-654-4524
>
> ኤች ስትሪት የአገልግሎት ማእከል
> (H Street Service Center)
> 645 H St. NE
> የስልክ ቁጥር: (202) 698-4350
> ፋክስ: 202-724-8964
>
> አናኮስትያ የአገልግሎት ማእከል (Anacostia Service Center)
> 2100 Martin Luther King Jr. Ave., SE
> የስልክ ቁጥር: (202) 645-4614
> ፋክስ፡ (202) 727-3527

አዲስ ፕሮግራምም አለ። ፓንዴሚክ-ኢ-ቢ-ቲ ወይም ፒ-ኢ-ቢ-ቲ (**Pandemic-EBT ወይም P-EBT**) ይባላል። ይህ ፓንዴሚክ ኢ-ቢ-ቲ የሚባለው በኮቪድ (COVID-19) ምክንያት በተከተለው የጤናና የደህነንት ችግር ምክንያት ትምህርት ቤቶች ስለተዘጉ፤ ከትምህርት ቤት ምግባቸውን በነጻ የሚያገኙ ለነበሩት ልጆችና ቤተሰቦቻቸው ተጨማሪ ምግብ እንዲያገኙ የሚያደርግ ነው።

የአገር ውስጥ ደህንነት ክፍል (DHS) ዌብሳይት ፈጥሯል website እንዲሁም ቤተሰቦች ወደ ወደ ፒ-ኢ-ቢ-ቲ P-EBT ለመደወል የሚያስችላቸውን የስልክ መስመር 202-868-6663 አዘጋጅቷል።

**በኮቪድ ምክንያት ስራዬን አላጣሁም ግን በቀን የምሰራባቸው ሰዓቶች ተቀንሰውብኛል።አሁን የማገኘው ገቢ ጎድሏል። አሁንም የስናፕና የቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ SNAP/TANF እርዳታ ላገኝ እችላለሁን?**

ይህ በሚያገኙት ገቢና ቤት ውስጥ በሚኖረው የሰው ቁጥር ላይ ይመረኮዛል።

ለስናፕ (SNAP) ፤ በዲስትሪክቱ፤ የገቢ መጠን (የማእከላዊ መንግስት ዝቅ ያለ ነው) ና ምን ያህል ጠቀሜታ እንደሚሰጥ ቀጥሎ ይሚገኘው ሰንጠረዥ ያስረዳል።

| የቤተሰብ ቁጥር | **ከፍተኛው ገቢ የወር ገቢ** | **የሚሰጠው ከፍተኛው እርዳታ** |
|---|---|---|
| 1 | $2,147 | $250 |
| 2 | $2,903 | $459 |
| 3 | $3,660 | $658 |
| 4 | $4,417 | $835 |
| 5 | $5,173 | $992 |
| 6 | $5,930 | $1,190 |

<u>የስናፕ ( SNAP) ጠቀሜታ ሕዳር 2021 ድረስ 15% ይጨምራል</u>

ለቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (TANF) ደግሞ የገቢ መጠንና የሚሰጠው ከፍተኛው ጠቀሜታ (ምንም ገቢ ለሌለው) እንደሚከተለው ነው፤

| **የቤተሰብ ቁጥር** | **ለማመልከት ብቁ ለመሆን የሚያስፈልግ የወር ገቢ** | **ቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (TANF)** ጠቀሜታ |
|---|---|---|
| 1 | $574 | $414 |
| 2 | $675 | $515 |
| 3 | $818 | $658 |
| 4 | $964 | $804 |
| 5 | $1,088 | $928 |
| 6 | $1,251 | $1,091 |

**የስናፕና የቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (SNAP እና TANF) ጠቀሜታዎች እስኪጀመርልኝ ስንት ግዜ ይፈጃል ?**

የሰብአዊ አገልግሎት ክፍል (Department of Human Services) የስናፕ (ማመልከቻዎን በ30 ቀናት ውስጥ ተመልክቶ ያገባድዳል። ይህም አስቸኳይ የምግብ እርዳታ ለማግኘት በሚከተሉት ምክንያቶች ብቁ

ከሆኑ ግን ጉዳዩ በ ሰባት ቀን ውስጥ ይገባደድሎታል፤ 1) ከ $100 ያነሰ ገንዘብ ካሎት ወይም የወር ገቢዎ ከ $150 ያነሰ ከሆነ ወይም 2) ለቤት ኪራይ፣ ለመብራት፣ውሃና ጋዝ በየወሩ የሚከፍሉት ገንዘብ በየወሩ ከሚያገኙት ገቢ ከበለጠ

የሰብአዊ አገልግሎት ክፍል (Department of Human Services ) የቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (TANF) ማመልከቻዎን በ45 ቀናት ውስጥ ያገባድዳል።.

አንዴ ለሁለቱም እርዳታዎች ያስገቧቸው ማመልከቻዎች ተቀባይነት ካገኙ፤ የሰብአዊ አገልግሎት ክፍል (Department of Human Services ) በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ የሚሰራ የጠቀሜታ ካርድ (Electronic Benefits Transfer ወይም EBT) በፖስታ ይልክሎታል።

**የስናፕና የቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (SNAP እና TANF) ጠቀሜታዎችን ማግኘት ስጀምር፤ ሌላ ገቢ ማግኘት ጀመርኩ፤ የጀመርኩትን የስናፕና የቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (SNAP እና TANF) ማግኘቴን እቀጥላለሁን?**

ይህ፤ ምን ያህል ገቢ አሁን በማግኘት ላይ መሆኖ ላይና የሚያገኙት ገቢ ከየት እንደሚመጣ ላይ ይመረኮዛል።

በስልክ ቁጥር (202) 727-5355 ወደ የሰብአዊ አገልግሎት ክፍል (Department of Human Services) ደውለው ይህንን የገቢ ለውጥ መንገር አለቦት። ከዚህም በኋላ የሰብአዊ አገልግሎት ክፍል (Department of Human Services) ምን ያህል እርዳታ ማግኘት እንዳለቦት ይወስናል። መነገር ያለባቸውና የሚሰጦትን ጠቀሜታ የሚወስኑት ገቢ ያገኙባቸው ምንጮች ፤ ከደሞዝ፣ ከስራ ሲወጡ ከመንግስት ከሚከፈለው ጠቀሜታ (unemployment benefits) ና ከሶሻል ሴኩሪቲ ያገኙዋቸው ገቢዎች ናቸው። የኤኮኖሚ ችግር ሲያጋጥም የሚሰጡ ክፍያዎች ወይም ለማበረታቻ ተብሎ ሚያዝያ 2020 እና ታህሳስ 2020 የጀመረው ክፍያና ለልጆች የሚሰጠው ገንዘብ በሰብአዊ አገልግሎት ክፍል( DHS) እንደ ገቢ አይቆጠርም።

**ለስናፕና ለቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (SNAP እና TANF) ሳመለከት ችግር ቢያጋጥመኝ የት ነው የምደውለው?**

በስልክ ቁጥር (202) 727-5355 ወደ ሰብአዊ አገልግሎት ክፍል (Department of Human Services) መደወል ይችላሉ።

መስመር ማግኘት ካቃቶትና አሁንም እርዳታ የሚያስፈልጎት ከሆነ፤ ወደ ሊጋል ኤድ (Legal Aid) በስልክ ቁጥር (202) 628-1161 ደውሉ ወይም አገለግሎት ለማግኘት ለማመልከት ወደ ኦንላይን online ይግቡ።

<u>የጤና ኢንሹራንስ</u> (Health Insurance)

**ስራዬን ሳጣ፤ የጤና ኢንሹራንሴንም አብሬ አጣሁ።የህዝብ የጤና ኢንሹራንስ ለማግኘት ላመለክት እችላለሁን?**

አዎን። በገቢዎ መጠንና በስደተኛነት ደረጃዎ ላይ የሚሞረከዙ አያሌ አማራጮች አሎት።

**ሜዲኬድ** (Medicaid) ፤ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውና አካለስንኩል የሆኑ የአሜሪካ ዜጎች፤ ህጋዊ የሆነ የመኖር ያ ፈቃድ ያላቸው ወይም የሆነ ዓይነት ህጋዊ ፈቃድ ያላቸው ሰዎች የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያደርግና የህክምና ወጪያቸውን የሚከፍል ፕሮግራም ነው። (ወደታች የሜዲኬድ አከፋፈል እንዴት እንደሆነ ይመልከቱ) ለማመልከት ደግሞ፤ ወደ ኦንላይን ወደ online through DC Health Link ገብተው ማመልከት ይችላሉ፤ ወይም ማመልከቻዎን application ወደሚከተለው አድራሻ ይላኩ፤

ዲሲ ሄልት ሊንክ (DC Health Link)
Department of Human Services
Case Records Management Unit
P.O. Box 91560
Washington DC 20090

ማማለከቻውም በአማርኛ፣ በስፓኒሽና በቻይናና በፈረንሳይኛ ቋንቋዎች ተዘጋጅቷል።

**አላያንስና** (Alliance) እና **የስደተኞች ልጆች ፕሮግራም** (Immigrant Children's Program) የተባሉ ፕሮግራሞች ደግሞ ሜዲኬድ የሚጠይቃቸውን የገቢ መጠን (የስደተኛ ጉዳይ ወይ ደረጃ እዚህ ላይ ግምት ውስጥ አይገባም) ላሟሉ አዋቂዎች የጤና ኢንሹራንስ (አላያንስ) ፤ ለልጆችም እንዲሁ የጤና ኢንሹራንስ የሚሰጡ ናቸው። ለእነዚህ የሚሞላው ማመልከቻም ለስናፕና ለቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (SNAP እና TANF) የሚሞላው ማመልከቻ ነው። በ online እና በ DC Access mobile app በመግባት ማመልከትና በ ፋክስ ወደ አገልግሎት ማእከል (Service Center) (ቁጥሩ ከወደ ታች ይገኛል) መላክ ይቻላል። ማመልከቻዎቹ በእንግሊዘኛ፣ በ ስፓኒሽ ና በአማርኛ ቋንቋዎች ተዘጋጅተዋል። በአካል ሂደውም መጽጠት ይቻላል ይህ ግን በአሁኑ ግዜ በጤና እክሉ ምክንያት አይደገፍም።

ኮንግሬስ ሃይትስ የአገልግሎት ማእከል (Congress Heights Service Center)
4049 South Capitol St., SW
የስልክ ቁጥር: (202) 645-4546
የፋክስ ቁጥር: 202-654-4524

ኤች ስትሪት የአገልግሎት ማእከል (H Street Service Center)
645 H St. NE

የስልክ ቁጥር: (202) 698-4350
የፋክስ ቁጥር: 202-724-8964

የአናኮስትያ የአገልግሎት ማእከል ( Anacostia Street Service Center)
2100 Martin Luther King Jr. Ave., SE
የስልክ ቁጥር: (202) 645-4614
ፋክስ: (202) 727-3527

**ለኢንስታካርት (Instacart) እቃ የማመላለስ ስራ በመስራት ትንሽ ገቢ ባገኝ፤ ግን የጤና ሽፋን ኢንሹራንስ፤ የነበረኝን ስራዬን ሳጣ፤ ኢንሹራንሴም አብሮ ስለሄደ፤ ሜዲኬድ ወይም አላያንስ ለማግኘት አሁንም ብቁ እሆናለሁን ?**

የሚከተለው ሰንጠረዥ የሜዲኬድና የአላያንስ ብቁነት ያሳያል፤

| የቤተሰብ ብዛት | ከ 65 ዓመት ዕድሜ በላይ ለሆኑና ስንክልና ያላቸው | አላያንስ (Alliance) | ልጆች የሌላቸው አዋቂዎች ሚዲኬድ ዕድሜ ከ21-64 | ሜዲኬድ ለወላጆችና ለወጣቶች ዕድሜ ከ19-20 | ሜዲኬድ ለነፍሰ ጡሮችና 18 ወይም ከዛ በታች ለሆኑ ወጣቶች |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | $1,063 | $2,126 | $2,232 | $2,296 | $3,391 |
| 2 | $1,437 | $2,874 | $3,018 | $3,104 | $4,584 |
| 3 | $1,810 | $3,620 | $3,801 | $3,910 | $5,774 |
| 4 | $2,183 | $4,366 | $4,584 | $4,715 | $6,964 |
| 5 | $2,557 | $5,144 | $5,370 | $5,523 | $8,167 |
| ለተጨማሪ የቤተሰብ አባል | +$373 | +$746 | +$783 | +$806 | +$1,190 |

ገቢዎ፤ ሜዲኬድና አላያንስ ከሚጠይቁት በላይ ከሆነና እርስዎ የአሜሪካ ዜጋ፣ ህጋዊ የመኖርያ ፍቃድ ያሎት፣ወይም ሌላ ህጋዊ ወረቀት ያሎት ከሆኑ ፤ በዲሲ የጤና ግንኙነት (DC Health Link) አማካኝነት በግል ኢንሹራንስ ውስጥ መመዝገብ ይችላሉ። ምን ያህል ገቢ እንደሚያገኙ ታይቶ፤ ለጤና ኢንሹራንስ የሚከፍሉትን ገንዘብ ዝቅ ሊደርሎት ይችል ይሆናል።

**የጤና ኢንሹራንሱ እስኪጀምር ድረስ ምን ያህል ግዜ ይፈጃል?**

የሰብአዊ አገልግሎት ክፍል (The Department of Human Services) የሜዲኬድና የአላያንስን ማመልከቻዎች አጥንቶ ለመጨርስ አብዛኛውን ግዜ 45 ቀናት ያስፈልገዋል።

**ሜዲኬድ ማግኘት ስጀምር፤ ሌላ ገቢ ማግኘት ጀመርኩ፤ ሜዲኬድ ማግኘቴን እቀጥላለሁን?**

ይህ የወረርሽኝ አደጋ እስካለ ድረስና ካለቀም በኋላ ላሉት 60 ቀናት፡ የጠና ኢንሹራንስ ማግኘቶን ይቀጥላሉ፤ ያጋጠሞትን የሆነ የሁኔታዎች ለውጥም ሪፖርት ማደርግ አይጠበቅቦትም። ይሁንና፤ ዲሲ፤ የወረርሽኙ በሽታ ካቆመም በኋላ፤ በሁኔታዎ ላይ የሆነ ዓይነት ለውጥ ካለ የምታገኙትን ብ የጤና ኢንሹራንስ ዓይነት ሊቀይር ስለሚችል፤ሁሌም ሪፖርት እንድታደርጉ ይጠይቃል። ምናልባትም ከሰብአዊ አገልግሎት ክፍል ወይም ከጤና ጥበቃ ክፍል ደብዳቤ ወይም ኢሜል ተልኮሎት እንደሆነም በደንብ ተከታተሉ።፡

**የጤና ኢንሹራንስ እንዳገኝ ሳመለክት ችግር ካጋጠመኝ የት ነው የምደውለው ?**

በስልክ ቁጥር (202) 727-5355 ወደ ሰብአዊ አገልግሎት ክፍል (Department of Human Services) ፤ ወደ ኡምባድስማን የጤና ጥበቃ መስርያ ቤትም (Office of the Health Care Ombudsman) በስልክ ቁጥር (202) 724-7491 መደወል ይችላሉ።

lመስመሩ አልገኝ ካሎት ደግሞና አሁንም እርዳታ የሚያስፈልጎት ከሆነ ከሊጋል ኤድ (Legal Aid) ጋር በስልክ ቁጥር (202) 628-1161 በመደወል ተገናኙ ወይም አገልግሎት ለማግኘት [online](online) አመልክቱ።

**<u>አቤቱታዎች</u>**

**የሰናፐ (SNAP) ፣ ታንፍ (TANF) ፣ አይዲኤ (IDA) ፣ ወይም የጤና ዋስትና ውሳኔዎች ላይ የማልስማማ ከሆነ እንዴት ይግባኝ መጠየቅ እችላለሁኝ?**

የይግባኝ ጥያቄዎችን ከአስተዳደር ጉዳይ ቅሬታ ሰሚ ቢሮ (Office of Administrative Hearings) (OAH) ጋር ኦንላይን (https://oah.dc.gov/node/148662) ወይም በስልክ (202) 442-9094 መጠየቅ ይችላሉ። በአካል ቀርበው ለሚያመለክቱ መስርያ ቤቱ እስከ ሕዳር 11 <u>ቀን 2021</u> ድረስ ዝግ ነው። ይግባኝ መጠየቂያ የመጨረሻው ማብቂያ ቀን 90 ቀናት ነው።

**<u>የስንክልና እርዳታ</u>** (Disability Assistance)

**ስራ መስራትን እጅግ ከባድ የሚያድረግ ስንክልና አለብኝ፤ ሊረዱኝ የሚችሉ ምንጮች አሉን?**

ከስራ የሚያግዳቸው ስንክልና ያላቸው ሰዎች ተጨማሪ የሴኩሪቲ ገቢ **Supplemental Security Income** (ኤስ-ኤስ-አይ SSI) እና/ወይም ሶሻል ሴኩሪቲ የስንክልና ኢንሹራንስ **Social Security Disability Insurance** ለማግኘት ማመልከት ይችላሉ። ኤስ-ኤስ-አይ (SSI) ፤ አነስተኛ ገቢ ወይም አነስተኝ የገቢ ምንጮች ላላቸው አካልሰንኩላን በየወሩ የሚስጥ የገንዘብ ክፍያ ነው። (ኤስ-ኤስ-ዲ-አይ (SSDI) ደግሞ ስራ ይሰሩ የነበሩ አሁን ግን መስራት ለሚያዳግታቸው አካለስንኩላን የሚሰጥ የገንዘብ ክፍያ ነው።

ለሁለቱም፡ ኤስ-ኤስ-አይ (SSI) እና ለኤስ-ኤስ-ዲ-አይ (SSDI) በስልክ ቁጥር 800-772-1213 በመደወል ወይም የኦንላይን ማመልከቻዎን online ገብተው ማመልከት ይችላሉ። በአሁኑ ግዜ ግን የሶሻል ሴኩሪቲ ጽህፈት ቤቶች በአካል ለመገናኘት ዝግ ናቸው።

ለኤስ-ኤስ-አይ (SSI) ያመለከቱ ከሆነ፡ ገቢዎ ዝቅተኛ ከሆነና በቤትዎ ውስጥ ለሚኖሩ ትናንሽ ልጆች እንክብካቤ የማያደርጉ ከሆኑ፤ **Interim Disability Assistance** (IDA) በመባል ለሚታወቀው ለዲሲ ልዩ የካሽ እርዳታ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። የዚህ ማመልከቻም ለ SNAP እና TANF እንዳስገቡት ማመልከቻ አንድ ዓይነት ነው። ይሄውም በተለያዩ ቋንቋዎች (በእንግሊዘኛ፣ በስፓኒሽና በአማርኛ ቋንቋዎች) ተዘጋጅቶ ቀርቧል። በኦንላይን online ማመልከት ይቻላል። ሞልተው ከጨረሱም በኋላ በኤች ስትሪት ወደ ሚገኘው ጽህፈት ቤት H Street Service Center (ቁጥሩ ወደ ታች በኩል የሚገኝ) ፋክስ ማድረግ ይችላሉ ወይም ወደዚሁ ጽህፈት ቤት በአካል ሄደው መስጠት ይችላሉ ግን ይህ ተቀባይነት የለውም።

> ኤች ስትሪት የአገልግሎት ማእከል (H Street Service Center
> 645 H St. NE
> የስልክ ቁጥር: (202) 698-4350
> የፋክስ ቁጥር: 202-724-8964

ሃኪሞ የህክምና ሁኔታዎን የሚያመልክት Medical Examination Report የተባለ ፎርም መሙላት ያስፈልገዋል። የአይ-ዲ-ኤ (IDA) ን ማመልከቻ ካለ ሃኪም ሪፖርት ልትሞሉ ይችላሉ ግን የሰብአዊ አገልግሎት ክፍል (Department of Human Services) ግን ካለ ሃኪም ሪፕርት ምንም እርዳታ አይሰጥትም።

**ያለኝ ስንክልና ቀኑን ሙሉ ለመስራት አዳጋች የሚያደርግብኝ ቢሆንም አንዳንድ ቀዳዳ መሸፈኛ ገቢ ለማግኘት ግን በከፊል ግዚያት ግን ልሰራ እችላለሁ። ይህም ሆኖ የSSI ወይም የSSDI እርዳታ ማግኘት እችላለሁን?**

የከፊል ግዚያት ስራ የሚሰሩ ከ SSIና ወይም ከSSD እርዳታ መቀበል ይችላሉ።

ሶሻል ሴኩሪቲ፤ አንድ ሰው የ SSI ና ወይም SSDI እርዳታ ለማግኘት ብቁ ነው ወይስ አይደለም ብሎ ውስኔ ላይ የሚደርሰው ምን ያህል ገቢ ያገኛል፤ ስንከላው ደግሞ ለመስራት ያለውን ዕድል ምን ያህል ያደናቅፋል የሚሉትን ጥያቄዎች በመጠቅና በሚያገኘው መልስ ነው። አንድ ሰው ብዙ ገንዘብ የሚያገኝ ከሆነ (ለምሳሌ አንድ ሰው በ 2020 በወር ከ$1,260 በላይ የሚያገኝ ከሆነ) ወይም ሶሽያል ሴኩሪቲ ያ ሰው ያለው ስንክልና ስራ ለመስራት አያደናቅፈውም ብሎ ከወሰነ ያ ሰው እርዳታ ለማግኘት ብቁ አይደለማ ማለት ነው።

አንድ ሰው SSI ለማግኘት አንዴ ብቁ ሆኖ ከተገኘ፤ ሶሻል ሴኩሪቲ፤ የሚያገኙትን ገቢ ግምት ውስጥ አስገብቶ በወር ምን ያህል የገንዘብ እርዳታ እንደሚሰጠው ይወስናል። በ 2020፤ አንድ ሰው ገቢው ከ $783 በታች ሲሆን ነው የገንዘብ እርዳታ የሚያገኘው።

አንድ ሰው SSDI ለማግኘት አንዴ ብቁ ሆኖ ከተገኘ፤ በወር የሚያገኘው ገቢ ከ $1,260 እስካልበለጠ ድረስ እርዳታ ሊያገኝ ይችላል። የሆነ ሰው በየወሩ የሚያገኘው የእርዳታ ገንዘብ፤ ከአሁን ቀደም ባገኘው ገቢ ነው የሚወሰነው።

ስለሚሰሩት ማንኛውም ስራና በየወሩ ምን ያህል ገቢ በማግኘት ለይ መሆኖን ለሶሻል ሴኩሪቲ ማሳወቅ እጅግ አስፈላጊ ነው።

### ከ SSI፤ SSDI፤ ወይም IDA ክፍያ ማግኘት መጀመር ምን ያህል ግዜ ይፈጃል?

የ SSI እና የSSDI ማመልከቻዎችን ለማጣራትና ለማጠናቀቅ ረዘም ያለ ግዜ ይፈጃል፤ ሶሻል ሴኩሪቲ (የህክምና ወረቀቶችን እስኪያሰባስብና ለመጀመርያ ግዜ ለገቡ ማመልከቻዎች ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ) አብዛኛውን ግዜ ወደ ስድስት ወራት ይወስድበታል። በየግዜው የጤንነቶን ጉዳይ (በተቻለ መጠን) መከታተል፤ የታከሙባቸውን ወረቀቶች መዝገብ መያዝና ሶሽያል ሲኩሪቲ በዚህ ቀን ይህን አቅርቡ ብሎ የሚልክሎትን መልእክት ማክበርና በግዜው መልስ መስጠት በጣም አስፈላጊነው።

የአይ-ዲ-ኤ ማመልከቻዎች በ60 ቀናት ውስጥ መጠናቀቅ አለባቸው። ይህ ግን በዚህ በያዝነው የወረርሽኝ አደጋ ምክንያት ሊራዘም ይችላል። የ IDA ማመልከቻዎ ተቀባይነት ካገኘ፤የእርዳታ ገንዘቡን ከማግኘትዎ በፊት ገንዘቡ እስኪፈቀድ ድረስ ተራ ይጠብቁ ይሆናል።

### ለ SSI፤ SSDI፤ ወይም IDA ሳመለክት ችግር ካጋጠመኝ የት ነው ይምደውለው?

ለ SSI እና ለSSDI፤ በስልክ ቁጥር (**800**) **772-1213** ወደ ሶሻል ሴኩሪቲ ሊደውሉ ይችላሉ።

ለ IDA፤ በስልክ ቁጥር **202**) **727-5355** ወደ ሰብአዊ አገልግሎት ክፍል (Department of Human Services) መደወል ይችላሉ።
መስመር ካላገኙና አሁንም እርዳታ የሚያስፈልጎ ከሆኑ፤ ወደ ሊጋል ኤድ (Legal Aid) በስልክ ቁጥር (**202**) **628-1161** ይደውሉ ወይም አገልግሎታችንን ከፈለጉ ኦንላይን online በመግባት አመልክቱ

<u>ስደተኞች ህዝባዊ ጠቀሜታ እንዲያገኙ የሚያስፈግ የብቁነት መለኪያ</u>

### የአሜሪካን ዜጋ አይደለሁም፤ ህጋዊ የሆነ ቪዛ ወይም የስራ ፈቀድ የለኝም። ቀደም ሲል ለተገለጹት የእርዳታ ፕሮግራሞች (ለምሳሌ ለSNAP፣ ለTANF፣ ለጤና ኢንሹራንስ ወይም ከስንክልና ጋር የተያያዘ እርዳታ) ብቁ ልሆን እችላለሁን?

SNAP (የምግብ እርዳታ) TANF (የገንዘብ እርዳታ) የስንኩላን እርዳታ (SSI) እና ሜዲኬድ (Medicaid) እርዳታ የሚያደርጉት ለአሜርካ ዜጎች፡ ህጋዊ የመኖርያ ወረቀት (ግሪን ካርድ) ላላቸው ሰዎች ወይም “ብቁ ለሆኑ ሰደተኞች” “qualified immigrants.” ነው። ወላጆቻቸው፤ እነዚህን እርዳታዎች ለማግኘት ብቁ ያልሆኑ ልጆች እርዳታዎቹን ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። አይ-ዲ-ኤ

(IDA) የሚሰጠው ኤስ-ኤስ-አይ (SSI) በማግኘት ላይ ላሉ ብቻ ነው።

SSDI ደግሞ ለአሜሪካን ዜጎችና በስራ ምክንያት አገር ውስጥ ያሉና ህጋዊ ህላዌ ወይም “lawfully present” የሚል ወረቀት ላላቸው ነው።

**በአላያንስ** (Alliance) በኩል የሚገኘው የጤና ኢንሹራንስ፤ በስደተኛ ሁኔታቸው ምክንያት ሜዲኬድ ለማግኘት ብቁ ላልሆኑ ሰዎች ነው።በስደተኛ ወረቀታቸው ምክንያት፤ ሜዲኬድ ለማግኘት ብቁ ያልሆኑ ልጆች **በስደተኛ ልጆች ፕሮግራም** (Immigrant Children’s Program) አማካኝነት የጤና ኢንሹራንስ ሊያገኙ ይችላሉ።

**ከሚሰጡት እርዳታዎች ውስጥ አንድ እንኳን ብቀበል፤ በዚህ (public charge rule) መሰረት አንጻሬ ሊሰራ ይችላልን?**

የትራምፕ አስተዳደር **የህዝብ ዕዳ ሕግ** (public charge rule ከአሁን በኋላ አይሰራም። ይህ የህዝብ ዕዳ ሕግ፤ በወቅቱ  በላዮ ላይ የሆነ ዓይነት ጠባሳ ሊያስከተል የሚችለው የህዝብ ገንዘብ እርዳታ የሚያገኙ ከሆነና የረጅም ግዜ ተቋማዊ  እገዛ ወይም እንክብካቤ የሚደረግሎት ከሆነ ብቻ ነው። በወቅቱ የገንዘብ ጠቀሜታ የሚባለው የቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ( TANF) የገንዘብ እርዳታ፤ የሶሻል ሴኩሪቲ ክፍያን ያጠቃልላል። ይሁንና  ስናፕ( SNAP )ን ወይም የምግብ ኩፖንን፣ ሜዲክሜድ( Medicaid )ን ቺፕን( CHIP ፤ ዊክ( WIC)ንና አሊያንስ( Alliance)ን ወይም ሌሎች የገንዘብ እርዳታዎችን አያጠቃልልም።

ከስደተኞች ጠበቃ ጋር በመስራት ላይ ከሆኑ፤ እርስዎም ይሁኑ ቤተሰቦ፤ ከህዝብ ማለትም ከመንግስት የምታገኙት ማንኛውንም እርዳታ ይንገሩት ወይም ይንገሯት። ስለዚሁ የህዝብ ዕዳ ህግ ተጨማሪ ጥያቄ ካሎት ከ ሊጋል ኤድ (Legal Aid) ጋ በስልክ ቁጥር (**202**) **628-1161** በመደወል ተገናኙ ወይም አገልግሎት ለማግኘት ኦንላይን online ይግቡ።

***

ጉዳዮን በሚመለከት ህጋዊ ምክር ቢያስፈግዎ፡ ከሊጋል ኤድ (Legal Aid) ጋር ተገናኙ። በአሁኑ ወቅት በኖርትዌስትና በሳውትኢስት (Northwest and Southeast) ያሉት መስርያ ቤቶቻችን ዝግ ናቸው በስልክና በኦንላይን ግን ክፍት ነን። አገልግሎታችንን ከፈለጉ በስልክ ቁጥር (202) 628-1161 ወይም በኦንላይን online ያመልክቱ።